# ለዓረና ትግራይና ለታንድ የተሰጠ ምላሽ

የዓረና ትግራይና የት.ዴ.ት/ታንድ መግለጫ እንዳለ አቅርበን አስነብበናችኋል። በዝርዝር ጉዳዩቹ ህወሓት መልስ እንዲሰጥበት ሁላችንም እንጠብቃለን።
የዓረና ትግራይና የት.ዴ.ት/ታንድ መግለጫ **ህገ-መንግስቱና ፌደራላዊ ስርአቱ ሳይሸራረፍ ተግባር ላይ በማዋል ሀገራዊ ዋስትና ማረጋገጥ ነው የሚቻለው"** መባሉ እንደድክመት ኮንኖታል። ችግሩ የት ላይ እንዳለ ቢዘረዝር መልካም ነበር። በአገራችንም ይሁን በመላው ዓለም ህገ መንግስት ካልተከበረ የሚከተለው ቀውስ ብቻ ነው። ህዝብ ሲፈልገው መሻሻል ይችላል። ከተሻሻለ በኃላም ያው በዝያው ህገ መንግስት መመራት ግዴታ ነው። በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ደግሞ ከፌደራሊዝም ሌላ የተለየ የመንግስት ስርዓት እርባና የለውም። ስለዚህ እነዚህ ሳይሸራረፉ ተግባር ላይ እንዲውሉ መታገል ምኑ ላይ እንደሚያስወቅስ ቢዘረዝር አስተማሪነቱ የጎላ እንዲሆን ያደርገዋል።

ሌላው በመግለጫው የተካተተው
**" ከሁሉም ማእዘን ጥቃት ተሰንዝሮብናል የሚለው የማስደንገጫ ደወል ህዝቡን በፍርሃት ድባብ ውስጥለመ ከተት የተጠነጠነ መሰሪ ሴራ እንጂ በህዝባችን ላይ ያነጣጠረ ጥቃት አይታይም፤ ሰርቶና አርሶ አዳሪው ህዝባ ችን ማንንም አልበደለም፣ማንኛውም ህዝብ በሱ ላይ አልተነሳም፡"** የሚለው የመግለጫው ክፍልም ኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ ወይም በሃገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በትግራይ ተወላጆች ላይ የተነጣጠረውን በደልና ሰቆቃ እንደ ኢምንት ያልቆጠረ ወገንተኝነት የጎደለው ሰው የጻፈው አስመስሎታል። በጎንደር ከተማ የተደበደቡ፣ንብረታቸው የተዘረፈና የተቃጠለ፣ ተወልደው ካደጉበት ምድር እንደ ባእድ ክብራቸውን በሚነካ መልኩ ሲባረሩ የህወሓት አመራር ስለነበሩ ነው እንዴ ? ወደ ትግራይ ምግብና ሸቀጣሸቀጥ እንዳይገባ መንገድ ዘግቶ መከልከል በህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ የተነጣጠረ በደል ነው እንዴ ? ርስት ናፋቂዎች የወልቃይትንና የራያን መሬት ማለት የትግራይን ግማሹን አካል ነጥቀው ለመውሰድ ህጋዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ውሳኔ ነው የሚያስፈልገው እያሉ ሽፍቶችንና በጎበዝ አለቃ ስም የተሰባሰበው የመንደር አውደልዳይ በግራም በቀኝም አሰልፎ ሲፎክር በህወሓት አመራር ላይ የተቃጣ ነው እንዴ ? ከዚህ በላይ በሁሉም ማእዝን ጥቃት ተከፍቶብናል የሚያስብል ምን ሊመጣ ይችላል ? ከዚህ በላይስ በትግራይ ህዝብ ላይ ከበባ ምን ሊታሰብ ይችላል ? በህዝባችን ላይ ያነጣጠረ ጥቃት አይታይም የተባለው ምን ለማለት ተፈልጎ ነው ? ጀግኖቹ የትግራይ ልጆች ቀፎው እንደተነካ ንብ በህብረት ስለተነሱ ነው እንጂ በሁሉም መአዝን ጥቃት ተከፍቶበት እንደነበር እንዴት ጥያቄ ውስጥ ይገባል ? መግለጫው እነዚህ ጉዳዮችንም ከበቂ በላይ የመረመረና የሚያብራራ የሚኮነኑትን በቅጡ የሚኮንን መሆን ይገባው ነበር ለማለት እንወዳለን።